# ብልቱ የተሰለበበት አሽከር በጌታው ብልት ይኩራራል

አብርሃም በየነ

ጓዜን ሸከፍ ሸከፍ ከብቴን ነዳ ነዳ
ምናልባት አንድ ቀን ጠላቴን ብጎዳ

አገሬን ሲከፋው ድሮ ድሮ እንጉርጉሮ ነበር የሚቀናው። “እዘጋው አለሁኝ ደጆን እንዳመሉ የት ሄደ ቢሏችሁ ከፍቶት ሄደ በሉ” ማለት የተለመደ ባህሪይው ነበር። ያ ባህሪይ በዛሬው ገበሬ ሰውነት ላይ ጨርሶ የለም። ተሰልቧል። አንድም በፍርሃት አንድም በድህነት። የህዝባችን በራስ የመተማመን ባህሪይ ካገሩ ሸሽቶ ጠፍቷል።

“አረ ልጅ ማሰሪያው አረ ልጅ ገመዱ ጎጆማ ምን አለው ዘግተውት ቢሄዱ” ይሉ የነበሩት አርበኞቻችን እነ አባ ኮስትር በላይ ዘለቀ፤ እነ ደ/ጃች ታከለ ወ/ሃዋርያት የፊተኛው በገመድ የኋለኛው በጥይት ተገደሉ። በባንዳ ንጉሥ።

እነርሱም አንቺ ሀገር ጀግና አይብቀልብሽ ብለው ስለረገሙን ይመስለኛል ከነርሱ ህልፈት በኋላ የተነሳው ያ ብርቅዬ ትውልድም በቀይ ሽብር የጥዋት ጤዛ ሆኖ እረገፈ። በደርግና በመኢሶን ፋሽሽት ካድሬዎች የተፈፀመው የጅምላ ግድያ ከደርግ በኋላ ባገሪቱ ያነገሰው ፍርሃት ጀግናና ጀግንነት በመሬቱ እንዳይኖር አድርጓል። መሬቱም አርጅቶ ሙጃና ማገጥ ማብቀል ጀምሯል። የህዝቡ ወኔም ተሰልቦ፦

አረ ጥራኝ ጫካው አረ ጥራኝ ዱሩ
ላንተም ይሻልሃል ብቻ ከማደሩ
ማለቱ ቀረና ሁሉም ሲከፋው እግሩ ወደ መራው አቅጣጫ ስደቱን ይያያዘዋል። የሚገርመው ነገር የሚሰደደው ህዝብ ከፍርሃቱ ጋር ካገር መውጣቱ ነው። በመሆኑም ጫካው ብቸኝነት አጥቅቶታል።

ዛሬ ዛሬ ፋኖ የሚናፍቅ ጫካና ጫካም የሚመኝ ጀግና ባገሩ ጠፍቷል። በምትኩ ግን የሞላና የተትረፈረፈው ነገር ወኔው የተሰለበ የህዝብ ብዛት ነው።

ከጠላቱ ጋር አብሮ ሲዶልት ሃፍረት የማይሰማው ህዝብ። ኢዴአፓን፡ እንድነት ለፍትህና ለዴሞካራሲን፡ ግንቦት ሰባትን....... ወዘተ ይመለከቷል።

የኢዴአፓ መሪዎች እነማናቸው ? የደርጉ ካድሬ ዶ/ር ሃይሉ አርአያና የወያኔው ካድሬ ልደቱ አያሌው።

የአንድነት መሪዎች የትናንቱ የኦፕዲዎ መሪ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና የወያኔው መስራች ፋሽሽት ስዬ አብርሃ ናቸው።

የግንቦት ሰባት መሪዎችም የወያኔው ካድሬ አንዳርጋቸው ፅጌና የበረከት ሰምኦን ጋሻጃግሬ የነበረው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ናቸው።

አንዳርጋቸው ፅጌ የወያኔን የዘር ትልም ለመድፈን በወያኔ ሾር ገብቶ “የአማራው ሕዝብ ከየት ወደ የት?” የሚል የራሱን ሌላ “የቡርቃ ዝምታ” የደረሰ ኮራኩር ወያኔ ነው።

ህዝብ ነጻነቱን ማግኘት የሚመኘው ከነዚህ የወያኔ ውዝፎች መሆኑ የብልቱን ስልበት ያረጋግጣል። ይህኑ ወኔውና ሃሞቱ ጥሎት የሸሸውን  ህዝብ ነው በጠላቶቹ በነ ሰየ አብርሃ ወኔና ሃሞት እንዲኩራራ የአንድነት ፓርቲ ወኪሎች ስብሰባ የጠሩት።

በዚህ በያዝነው ወር ሶስት ድርጅቶች በተከታታይ ወደ አትላንታ ጎራ ብለው ነበር።

የወያኔው መስራች ግደይ ዘራፂወንና ዶ/ር ሙሉጌታ ሰዩም ቁጥራቸው ከሃያ እስከ ሃያ ሰባት ለሚሆኑ አትላንታውያን ዲስኩር ደስኩረው ሄዱ። እነርሱን ተከትሎም ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በዶ/ር ዜሮ (ጌታቸው በጋሻውን) ታጅቦ የኦነግን ኢትዮጵያዊነት ሊያስመሰክር ጎራ አለ።

ኦነግ ግን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይለውጣልን? ሲል ማንነቱን አረጋገጠልን። የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን የኦነግ አሽከርነትም ማህተም መትቶበት ተመለሰ።

የኦነጉ ተወካይ “እናንተ የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ አለን ልትሉ ትችላላችሁ” (ወደነ ብርሃኑ እያማተረ)  “እኛ ግን የምናውቀው ከሚኒሊክ ጀመሮ የነበረውን የመቶ ዓመት ታሪክ ነው” ሲልም በቤቱ ውስጥ ወፍ ለቅማ እስክትወጣ ህዝቡን ጸጥ አሰኘው።

ወይ ከሁለቱ ዶክተሮች ወይ ከተሰብሳቢው ህዝብ ለንግግሩ ተቃውሞ ለማቅረብ የከጀለ ማንም አልነበረም። እድምተኛው ወንድነቱ መሰለቡን ለኦነግ ባደባባይ አምኖ ተበተነ።

ሁለቱ ዶክተሮችም የኢትዮጵያ ታሪክ የሶስት ሺህ ዘመን መሆኑ ቀርቶ የመቶ ዓመት ታሪክ መሆኑን ለተሰብሳቢው አስጨብጠው ወደ መጡበት ተመለሱ።

የኦነጉም ተወካይ “ጭዋነት” በተላበሰ ፍርሃት አትላንታ ላይ ጀግኖ ወጣ።

ስዬ አብርሃም ከነ ብርሃኑ የተረፈውን ኢትዮጵያዊ ወኔ ለማፅዳት እግር በእግር ተተካ። “የድሮው መከላከያ ሚኒስቴር” በሚል ማስታወቂያ እድምተኛም ታደመለት።

የስዬ መከላከያ ሚኒስተርነት ለማስታወቂያ መሳሂብነት መመረጡ ወኔ ለሸሸው ህዝብ ወደር የማይገኝለት ኢትዮጵያዊ ጀብዱ መሆኑ ነው።

የስየ አብርሃ ጀብዱ ቢዘረዘር በራሱ አንድ መደብል ስለሚወጣው ለዛሬው ፍጆታ ጨልፌ ጥቂቱን ላስታውሳችሁ፦

- ወያኔ የወልቃይትን መሬት ሲቆጣጠር  በወያኔ ሰራዊት ታፍነው ወደ ትግራይ ተወስደው ደብዛቸው ጠፍቶ ለቀሩት  ስምንት መቶ ሰምኒያ ወልቃይቴዎች ተጠያቂው በወቅቱ የወያኔ ጦር አዛዥ የነበረው ሰየ አብርሃ ነበር።

- ቋራ ላይ ተማርከው በወያኔ ደብዛቸው ጠፍቶ የቀሩት እነ ፀጋዬ ገ/መድህንና ሌሎቹም የኢሕአፓ መሪዎች በስየ አብርሃ ትዕዛዝ ነበር።

- በጎንደር አደባባይ እየሱስ በግፍ የተጨፈጨፉት ምእመናን ሰየ አብርሃ ይመራው በነበረው የጦር ሃይል ነበር።

- በዚያው ዓመት በቋራ ሽመል ሊቆርጥ ድንበር ጥሶ የመጣውን የሱዳን ጦር ለምን ተዋጋችሁ? ብሎ በግፍ ያስጨፈጨፋቸው የያኔው መከላከያ ሚኒስቴር ስየ አብርሃ ነበር።

- የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የግብጹን ተወላጅ የቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊን አዲስ አበባ መግባትና የኤርትራን መገንጠል ተቃውመው ሰልፍ ሲዎጡ በጠይት ያሳጨዳቸው ሰየ አብርሃ ነበር።

- በወተር፤ በአራካና በበደኖ አማራዎች ከነ ህይዎታቸው በኦነግ ካድሬዎች በገደል እየተወረወሩ ሲገደሉ የመከላከያ ሚኒስቴር የነበረው ሰየ አብርሃ ነበር።

- አርባ ሶስት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን የአማራ ትምክህተኞች ተብለው ከስራቸው ሲባረሩ የመከላከያ ሚኒስቴር የነበረው ስየ አብርሃ ነበር።

- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፓይለቶች አገር እየጣሉ ለጠላቶቻችን ለአረቦች ግልጋሎት ለጋሽ እንዲሆኑ የተሰደዱት ስየ አብርሃ የአየር መንገዱ የቦርድ ሊቀመንበር በነበረበት ወቅት ነበር።
-

የድሮ መከላከያ ሚኒስቴርነቱ የጥሪ የማስታወቂያ መሳሂብ ሆኖ መቅረቡ ወንጀሉ አኩሪ ታሪኩና ትውፊታዊ ጀብዱው ሆኖ ኢትዮጵያውን እንዲኮሩበት ሰየ ተጋበዘ።

የስየ ፎቶ ያለበትን የመግቢያ ትኬት ለህዝብ ሊሸጡ ሲከጅሉም አንድነቶች ስልብነታቸውን በስየ ወንድነት አረጋግጠዋል።

በነዚህ ስልቦች ጋጋታ የተጨናነቀችው አትላንታ የፖለቲካ ቂጥኝ መናኸሪያ ሆና ሰንብታለች። ይህችም ከተማ ሆና ቂጥኝ አፈራች እንዲሉ።

EthioLion.Com

ደግነቱ ሁሉም ጎብኙዎቿ ወርዷዎች ናቸው። እንደሚታወቀው ወርዷዎች ስለማይወልዱ ሴቶቹም ቢያመነዝሩ ወንዶቹም ቢያልሉ ዘማዊነታቸው ስጋት አይኖረውም።

መጋቢት 2004

»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»//»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»

EthioLion.Com